# “ያለምንም ርህራሄ ... እርምጃ እንዲወስድ” ኃይለማርያም ደሳለኝ

**እንዴት ጠቢብ፣ እንዴት ጀግና፤**

**እንዴት ይጥፋ ደፋር፤**

**በኢትዮጵያ ምደር?**

**ብሎ የሚመክር፤**

**አንተን ከሚያጠፋ ከቶ አትደራደር።**

ሁሉም ተነካክቶ በኩርማን እንጀራ

ወጣት ሽማግሌው ሲጠበስ በጥይት፣

ከፋኝ ብሎ ሲሸፍት፣ አስከትሎ ወጣት፣

ትግሉ ሲቀጣጠል ምን ድል አስገኘና ነው፣

ማነው ይህ አታላይ፣ ትጥቅ ፈታሁ ያለው?

ሕሌናውን ሽጦ ለኩርማን እንጀራ

ከወያኔ ጋራ የተደራደረው?

ወልቃይትን ለትግሪ ለጥፎ ሲያስጨርስ

ማነው ያ ሰላቢ ያኔ የሸፈተው፤

የህዋት ቅጥረኛ አማራን ከአረሞ

ለሃያ አምሥት ዓመት ሲያጣላ የኖረው፤

ዚሪ ምን አገኘና ነው፣ ትጥቅ ፈታሁ ያለው።

**እንዴት ጠቢብ፣ እንዴት ጀግና፤**

**እንዴት ይጥፋ ደፋር፤**

**በኢትዮጵያ ምደር?**

**ብሎ የሚመክር፤**

**አንተን ከሚያጠፋ ከቶ አትደራደር።**

በጥይት እሩምታ ቀን ከሊት ሲገደል

ወጣት ሽማግሌ በጎጃም፣ በጎንደር፤

በኦረሞም መንደር።

እሥር ቤትም ሳይቀር በሳት እንዲያ ሲጋይ፣

ማነው ይህ አይን አውጣ፣ እፍረት የለውም ወይ፤

ትናንት ሽፈትሁ ብሎ ዛሬ ትጥቅ ፈታሁ ባይ?

ላንድ ጠርሙስ ቧድካ ለኩርማን እንጀራም ለውጦ የሚበላ፣

የወገኖቹ ደም ጉሮሮ አለስላሽ መሰለው ወይ ጠላ።

ትላንት ሽፈትሁ ባይ

ዛሪ ትጥቅ ፈታሁ ባይ

በባሩዱ እሳት ካጋዩ በኋላ፣

ምን እራዕይ ታየው፣ ምንስ አመካከረው

ከቡድድኖቹ ጋር ለምንስ ጀመሩ፤

ዛሬስ ምን አገኙ በምንስ አሰሩ?

ትላንት በዱር ገደል ከፋኝ ሲል የነበር፤

ዛሬ ከወያኔ የሚደራደረው በወገኖቹ ደም
እንዲት ጀግና፤ እንዲት ጠፋ ደፍር?

በምንም አይሆንም ብሎ የሚናገር።

**እንዲት ጠቢብ፣ እንዲት ጀግና፤**

**እንዲት ይጥፋ ደፋር፤**

**በኢትዮጵያ ምደር?**

**ብሎ የሚመክር፤**

**አንተን ከሚያጠፋ ከቶ አትደራደር።**

ይቅርታን ጠይቆ ቃል ኪዳን ካልገባ

ደግሞ እንደ ገና ዘርህን እንዳያጠፋ

ምን አለህ ዋስትና፤

እንኳን ገደላና እንዳይደበድብህ በያዘው ቀጠና።

© ለምለም ፀጋው፣ ዘር ለማጥፋት የሚያቅዱን፣ ጥላቻንም ለሚያስተምሩ በመቃወም

መስከረም 19፣ 2009 (September 29, 2016)